# የገንዘብ ሚኒስቴር

# ለጤና ዘርፍ ተግባራዊ የሚሆን የቻናል-2 ፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ

# ቁጥር 979/2016 ዓ.ም

ጥር 2016 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

## ለጤና ዘርፍ ተግባራዊ የሚሆን የቻናል-2 ፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ

## ቁጥር 979/2016 ዓ.ም

የጤናው ዘርፍ የልማት እቅዶችን ለማስፈጸም ከለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ ገንዘብ አስተዳደር እና አጠቃቀም ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ጠንካራ የቻናል-2 ፋይናንስ የአስተዳደር እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን በመዘርጋት በጀቱ በአግባቡ እና ለታለመለት ዓላማ እንዲውል እና ለክልል ጤና ቢሮዎችና አስፈፃሚዎች የሚተላለፈው ገንዘብን በወቅቱ ማወራረድ በማስቻል ወጭ ቆጣቢ እና ውጤታማ የሆነ የፋይናንስ አጠቃቀም ስርዓትን በማጎልበት ተጨማሪ ሀብት ማስገኘት እንዲቻል ለማድረግ፣

የቻናል-2 ፋይናንስን የሚጠቀሙ የተለያዩ ተቋማት ጥራቱን የጠበቀ እና ወቅታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት የሚያቀርቡበትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ግልጽነት እና ተጠያቂነትን በማስፈን በፕሮግራም እና በፋይናንስ አስተዳደር መካከል የተናበበ እና የተቀናጀ አሰራር በመዘርጋት ለወጣው ወጭ ተመጣጣኝ ውጤት ማስገኘት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/ 2001 አንቀጽ 75 መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

1. **አጭር ስያሜ**

   ይህ መመሪያ *" ለጤና ዘርፍ ተግባራዊ የሚሆን የቻናል-2 ፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 979/2016"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1/ "**የቻናል-2 ፋይናንስ**" ማለት ከለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ ገንዘብ ሆኖ በቀጥታ ለጤና ሚኒስቴር ገቢ የሚሆን እና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚተዳደር ገንዘብ ነው፤

   2/ "**ጤናው ዘርፍ የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ፈንድ**" ማለት ከተወሰኑ ለጋሽ ድርጅቶች የሚሰበሰብ ገንዘብ ሆኖ በሚኒስቴሩ ቅድሚያ ለተሰጣቸው የጤና ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚውል የቻናል - 2 ፋይናንስ ቋት ነው፡፡

   3/"**ተቋም**" ማለት የቻናል-2 ፋይናንስ የሚተላለፍላቸው የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያጠቃልላል፤

   4/ "**ሚኒስቴር እና ሚኒስትር**" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የጤና ሚኒስቴር እና የሚኒስቴሩ ሚኒስትር ነው፤

   5/ "**የበላይ ኃላፊ**" ማለት ሚኒስትሩን ወይም ሚኒስትር ዴኤታን ያጠቃልላል፤

6/ “**የስራ ክፍሎች**” ማለት በሚኒስቴሩ ስር የተዋቀሩ የተለያዩ የስራ ክፍሎችን ያጠቃልላል፤

7/ “**ክልል**” ማለት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 47 የተመሰረተ ማንኛዉም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

8/ “**ገንዘብ ቢሮ**” ማለት የክልል እና የከተማ መስተዳድሮች የገንዘብ ቢሮ ነው፤

9/ “**ሰው**” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

10/ በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለ) እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንቡ ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥም በእነዚህ ሕጎች የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤

11/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በቻናል-2 ፋይናንስ፣ የቻናል-2 ፋይናንስን ስራ በሚያውሉ የጤና ሚኒስቴር የተለያዩ የስራ ክፍሎች እና የቻናል-2 ፋይናንስ በሚተላለፍላቸው ክልሎችና ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የቻናል-2 ፋይናንስ አስተዳደር

4. **ስለ ቻናል-2 ፋይናንስ ድልድል**

1/ የጤና ሚኒስቴር ዓመታዊ በጀት በሚያዘጋጅበት እና ለክልል ጤና ቢሮዎች የበጀት ድልድል በሚያደርግበት ወቅት የበጀት ዓመቱን የጤና ሴክተር የትኩረት አቅጣጫ፣ ያለፉት ዓመታት አፈፃፀም፣

የፌዴሬሽን ም/ቤት የፌዴራል ድጋፍ ቀመርን፣ የበሽታ ስርጭትን፣ የህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ ክስተቶችን፣ የተጎጂ/የተጠቃሚ ማህበረሰብ ክፍሎችን ሁኔታ እና/ወይም ሌሎች መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

2/ የጤናው ዘርፍ የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ በጀት ሲደለደል ዋና የትኩረት አቅጣጫው ለህክምና መሣሪያዎች እና አቅርቦቶች መሆን አለበት፡፡

## 5. ስለ በጀት ክለሳ እና ዝውውር

1/ ሚኒስቴሩ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ከለጋሾች የሚያገኝ ከሆነ ወይም የተመደበው በጀት በታቀደለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራ ላይ ካልዋለ ወይም የትኩረት አቅጣጫ ለውጥ ካጋጠመ የበላይ ኃላፊው የበጀት ዝውውር ወይም ክለሣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2/ ለክልል ጤና ቢሮዎች ወይም የተለያዩ ተቋማት የተላለፈው ገንዘብ በተለያየ ምክንያት ለታለመለት ዓላማ በታቀደው ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ ካልዋለ ወይም ተርፎ ከተገኘ ክልሎች ወይም ተቋማት ሥራ ላይ ካልዋለው በጀት ውስጥ እስከ 10 በመቶ የሚሆነውን ገንዘብ በማዛወር ተያያዥነት ላለው ዓላማ መጠቀም ይችላሉ፡፡

3/ የክልል ጤና ቢሮዎች ወይም ተቋማት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት በጀት ሲያዛውሩ ስለማዛወራቸው ለሚኒስቴሩ ማሣወቅ አለባቸው፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ጤና ቢሮዎች ወይም ተቋማት ከ10 በመቶ በላይ ለማዞር የሚኒስቴሩን ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡

## 6. የበጀት መጠቀሚያ ጊዜ እና ተመላሽን ስለማሳዎቅ

1/ ለክልል ጤና ቢሮዎች ወይም ተቋማት የሚተላለፍ በጀት በጀቱ በተላለፈበት የበጀት ዓመት ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡

2/ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ በጀት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ተደርጎ ተመላሽ እንዲደረግ ወይም በቀጣይ ዓመት ከሚመደበው በጀት ላይ ተቀናሽ መደረግ አለበት፡፡

3/ በዚህ ዓንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ተመላሽ የሚደረገው ወይም ለሚቀጥለው በጀት ዓመት ታሳቢ የሚደረገው በባንክ ወይም በካዝና የተገኘ ጥሬ ገንዘብ ነው፡፡

4/ ሚኒስቴሩ ጥቅም ላይ ያልዋለን በጀት በቀጣይ ዓመት ለክልሉ ወይም ለተቋማት የሚላክለት በጀት ላይ ታሣቢ ሊያደረግ ይችላል፡፡

## 7. ገንዘብ ስለ ማስተላለፍ

1/ ለክልል ጤና ቢሮዎች ወይም ተቋማት ገንዘብ እንዲተላለፍ የሚጠይቅ የስራ ክፍል፡-

ሀ) የገንዘብ ማስተላለፍ ጥያቄ ማቅረብ እና ማስተላለፍ የሚችለው በሩብ ዓመት ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

ለ) ከላይ በፊደል ተራ ቁጥር “ሀ” ስር የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የተለያዩ የዘመቻ ስራዎች በሚኖሩበት ጊዜ እንደ ዘመቻው እቅድ የሚተላለፍ ይሆናል፤

ሐ. ወረርሽኝ፣ የጎርፍ፣ የድርቅ ወይም ሌሎች የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች በሚከሰቱበት ወቅት ምላሽ በፍጥነት ለመስጠት እንዲቻል ገንዘብ በማንኛውም ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

መ) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርብ የገንዘብ ማስተላለፍ ጥያቄ የሚተላለፈውን የገንዘብ መጠን፣ የሚከናወኑ ዝርዝር

ተግባራትን፣ የገንዘቡን ምንጭ፣ ተግባሩ የሚፈፀምበትን ጊዜ እና ገንዘቡ የሚወራረድበትን ጊዜ የያዘ መሆን አለበለት፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአቅም በላይ የሆነ አስገዳጅ ሁኔታ ካልተፈጠረ እና ይህም በበላይ ኃላፊ ካልተፈቀደ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ከሚያዝያ እስከ ሰኔ ባሉት ወራቶች ውስጥ በጀት ማስተላለፍ አይቻልም፡፡

3/ ለግንባታ ስራ አገልግሎት እና ለሌሎች የካፒታል ፕሮጀክቶች የሚውል በጀት የሚተላለፈው እንደ ፕሮጀክቶቹ ልዩ ባህሪ እንደ ሁኔታው አስፈላጊነት በበላይ ኃላፊ ሲጸድቅ ብቻ ነው፡፡

4/ በዚህ መመሪያ መሰረት በተለይም ለጤናው ዘርፍ የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ የሚመደበው በጀት የሚተላለፍታቸው የክልል ጤና ቢሮዎች እና ተቋማት በአባሪ ቁጥር ሁለት የተመለከቱት ይሆናሉ፤ ሆኖም ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በልዩ ሁኔታ ለተጨማሪ ተቋማት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

5/ ለጤናው ዘርፍ የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ የሚመደበው በጀት የተላለፈለት የክልል ጤና ቢሮ ወይም ተቋም በወረዳ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ የማስፈጸሚያው በጀት ግን በቀጥታ ለወረዳ አይተላለፍም፡፡

## 8. <u>የበጀት ማስተላለፊያ መመዘኛ መስፈርቶች</u>

1/ ለክልል ጤና ቢሮዎች ወይም ለተቋማት የሚተላለፈው የበጀት መጠን እና ዝርዝር ሁኔታ የሚወሰነው በዚህ መመሪያ አባሪ-1 ላይ በሰፈረው የመመዘኛ መስፈርት መሰረት ይሆናል፡፡

2/ በመመዘኛ መስፈርቱ መሰረት በየሩብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ምዘና ይካሄዳል፤ የዚህንም መረጃ ሚኒስቴሩ የሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በሁለት ሣምንት ውስጥ በማጠናቀር ለበላይ ኃላፊ እና ስራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል እንዲሁም ለክልሎች ይኸው ይገለጻል፡፡

3/ በበጀት ዓመቱ የታቀደው የገንዘብ ድጋፍ የሚተላለፈው በአባሪ - 1 ላይ በተቀመጠው የመመዘኛ መስፈርት በሚገኘው አጠቃላይ ውጤት መሰረት ሆኖ ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡-

ሀ) ከ90%-100% ያገኘ የክልል ጤና ቢሮ ወይም ተቋም ከታቀደው በጀት 100% እንዲተላለፍለት ይደረጋል፤

ለ) ከ75% - 89% ያገኘ የክልል ጤና ቢሮ ወይም ተቋም ከታቀደው በጀት ውስጥ 75% እንዲለቀቅለት ይደረጋል፤

ሐ) ከ51%-74% ድረስ ያገኘ የክልል ጤና ቢሮ ወይም ተቋም ከታቀደው በጀት ውስጥ እስከ 50% ድረስ ብቻ እንዲለቀቅለት ይደረጋል፤

መ) ከ50% - 25% ያገኘ የክልል ጤና ቢሮ ወይም ተቋም ከታቀደው በጀት ውስጥ 25% ይተላለፍለታል፤

ሠ) ከ25 በታች ያገኘ የክልል ጤና ቢሮ ወይም ተቋም ምንም አይነት ገንዘብ አይተላለፍለትም፡፡

4/ ከአንድ ዓመት በላይ የሆናቸውን ሂሣቦች በአንድ ዓመት ውስጥ በተደረገ ተከታታይ ምዘና መሻሻል ያላሣየ የክልል ጤና ቢሮ ወይም ተቋም ያልተወራረደው ሂሳብ በቀጣይ በጀት ዓመት ከሚመደብላቸው በጀት ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

### 9. የጤና ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

ሚኒስትር መ/ቤቱ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1/ በበጀት የተደገፈ ዓመታዊ እቅድን ያዘጋጃል፤

2/ በበጀት ዝግጅት እና ክለሣ ወቅት የክልል ጤና ቢሮዎች እንዲሣተፉ ያደርጋል፤

3/ ለክልል ጤና ቢሮዎች ወይም ተቋማት ሊተላለፍ የሚገባውን ገንዘብ በወቅቱ ያስተላልፋል፤

4/ የተላለፈውን ገንዘብ ወይም ሀብት በተመለከተ የፕሮግራም አፈጻጸምና የገንዘብ አጠቃቀሙ የተጣጣመ መሆኑን ይከታተላል፤

5/ ለክልሎችና ሌሎች ተቋማት የተላለፈው ገንዘብ ስላስገኘው ውጤት፣ ስለአፈጻጸሙ፤ ሂሳቡ ስለመወራረዱ ይገመግማል፤

6/ የቻናል-2 ሂሳብ አስተዳደር ስርዓት ለማሻሻል በገንዘብ ሚኒስቴር የወጡና ስራ ላይ ያሉትን የፋይናንስ አሰራሩ መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ የሂሳብ አስተዳደር ማኑዋል ያዘጋጃል አፈጻጻሙም ይከታተላል፤

7/ የሁሉም ፕሮግራም ሂሳቦች የበጀት ዓመታቸውን ጠብቀው እንዲዘጉ እና ኦዲት እንዲደረጉ እንዲሁም የኦዲት ሪፖርቱ ለለጋሾች በእቅዱ መሰረት እንዲደርስ ያደርጋል፤

8/ በየዓመቱ የሚዘጋጀውና ለተቋማት ሊተላለፍ የሚችለውን በጀት ለሚመለከታቸው ተቋማት በማሳወቅ ግልጽነት ያለው አሰራር ይዘረጋል እንዲሁም የተመደበው ግራንት ለታለመለት ዓላማ እና በወቅቱ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

9/ ከለጋሽ ድርጅቶች ቃል የተገባው ገንዘብ በመከታተል በወቅቱ ወደ የሚኒስቴሩ የባንክ ሂሳብ እንዲገባ መከታተልና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ይከታተላል፤

10/ከዓመታዊ የጤናው ዘርፍ እቅድ ጋር በማናበብ የመንግስት የልማት እቅዶች እና የበጀት ዑደት ተከትሎ የበጀት እቅድ ያዘጋጃል፤ የበጀት ክፍተት ያለባቸውን ተግባራትም ይለያል፤

11/በበጀት ዓመቱ ለእያንዳንዱ የክልል ጤና ቢሮ እንዲሁም ሌሎች ተቋማት የተመደበውን (ሊተላለፍ የሚችለውን) በጀት ታሣቢ በማድረግ የመግባቢያ ሰነዱ (MoU) በበጀት ዓመቱ ነሐሴ ወር የመጀመሪያው ሣምንት ላይ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት እንዲፈረም ያደርጋል፤

12/በጀት ዓመቱ እንዲገዙ የሚፈለጉ የሕክምና ግብዓቶች ትንበያ እና ግምት ዝግጅት ያስተባብራል፤ በበላይ ኃላፊ የፀደቀ ጥቅል የግዥ እቅድ ከነበጀት ምንጩ ለኢትዮጵያ መድሀኒት አቅርቦት አገልግሎት ያሳውቃል፤

## 10. የኢትዮጵያ የመድሀኒት አቅርቦት አገልግሎት ተግባርና ኃላፊነት

የኢትዮጵያ መድሀኒት አቅርቦት አገልግሎት የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖርበታል፡-

1/ በተላከለት የግዥ እቅድ መሰረት የግዥ ትእዛዝ እና የክፍያ ትእዛዝ (purchase Order-PO) ደረጃ ላይ በማድረስ ገንዘብ እንዲለቀቅለት ይጠይቃል፤

2/ ከሚኒስቴሩ በሚተላለፍለት ገንዘብ ግዥውን ፈጽሞ ከስድት እስከ ዘጠኝ ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ ከተሟላ ማስረጃ ጋር ሂሳቡን ማወራረድ አለበት፤

3/ ለግዥና ተያያዥ ተግባራት የተላለፈለትን ሂሳብ በማስታረቅ በየወሩ የፋይናንስና የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

4/ ከሚኒስቴሩ የቀረበለትን የግዥ ጥያቄ በተመለከተ የግዥው ሂደት ያለበት ሁኔታን (ግዥው በጨረታ ሂደት፤ የባንክ መተማመኛ ሰነድ (Letter of Credit) ሂደት ላይ የደረሰ፤ ሂደቱ ተጠናቆ በከፊል እቃው ገቢ ሆኖ በከፊል የቀረ ጭነት የሚጠብቅ (Partial shipment) የግዥ ሂደቱ ገና ያልተጀመረውን) በማመላከት ዝርዝሩን የሚያሳይ ሪፖርት በየሦስት ወሩ በቋሚነት መላክ አለበት፤

5/ በፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች የቀረጥ እና ታክስ ሂሳቦች በተስተናገዱ በአንድ ወር ውስጥ ዝርዝር ማስረጃ ያቀርባል፤

6/ የግዥ ሂደቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ የባንክ መተማመኛ ሠነዶችን በማቅረብ ማዘጋት ይጠበቅበታል፤

7/ ለጤና ፕሮግራሞች አገልግሎት የተገዙ ግብዓቶች ሚኒስቴሩ በሚሰጠው የስርጭት ዝርዝር መሠረት ለተጠቃሚዎች ለመድረሱ በየሦስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል።

## 11. የክልል ጤና ቢሮዎች እና ተቋማት ሀላፊነት

የክልል ጤና ቢሮዎችና ተቋማት የሚከተሉት ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡

1/ በቻናል ሁለት የፋይናንስ አስተዳደር ዙሪያ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና አሰራሮችን በማስተካከል ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር እንዲሰፍን ማድረግ፤

2/ የተራድኦ ገንዘብ በተያዘው እቅድ መሰረት ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል ያደርጋሉ፣

3/ ከቻናል ሁለት የሚተላለፍላቸውን ገንዘብ ከተላለፍላቸው ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ያወራርዳሉ፤

4/ ከላይ በአንቀጽ 11 ንዑስ ቁጥር 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለግንባታ እና ካፒታል ዕቃ ግዥ የተላለፉ ገንዘቦችን በሚመለከት የግንባታ እና የግዢውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የማወራረድ ግዴታ አለባቸው፤

5/ ስራ ላይ የዋለዉ ገንዘብም አስፈላጊና ህጋዊ ደጋፊ የሂሳብ ማስረጃዎች እንዲደገፍ በማድረግ ጥራታቸዉን የጠበቁ የሂሳብና የፕሮግራም ሪፖርቶች በየወሩ ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ፣

6/ የዓመቱ የተላለፈው ገንዘብ እና ክንውን እንዲሁም የፋይናንስ እና ፕሮግራም እቅድን ከአፈጻጸም ሪፖርት ጋር በማነጻጸር በየሩብ ዓመቱ እንዲላክ ያደርጋሉ፤

7/ ከቻናል ሁለት የተላለፈውን ገንዘብ በአግባቡ በመመዝገብ በየወሩ የሂሣብ ማስታረቅ በማከናወን የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ፣ የሂሣብ ሚዛን፣ የተሰብሣቢና የተከፋይ ዝርዝር ወርሃዊ ሪፖርቶችን ያቀርባሉ፤

8/ ከ ጤናው ዘርፍ የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ የሚላከው ገንዘብ ለወረዳዎች እንዲሁም ዞኖች እንዳይወርድ ያደርጋሉ፤ ሆኖም በወረዳዎች የሚከናወኑ ስራዎች በክልሉ አማካኝነት ሳይጓደሉ እንዲከናወኑ ያደርጋሉ፤

9/ ከላይ በአንቀጽ 12 ንዑስ ቁጥር 8 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ጤና ቢሮዎች ከተላለፈላቸው ገንዘብ ላይ በስራቸው ለሚገኙ ሆስፒታሎች ወይም የሞያ ማኅልበቻ ማዕከላት ገንዘብ ሊያስተላልፉ ይችላሉ፤ ሆኖም ያስተላለፉት ገንዘብ በትክክል ስራ ላይ መዋሉ፣ የተፈለገው ውጤት ማስገኘቱ የመከታተል እንዲሁም ከላይ በአንቀጽ 12 ንዑስ ቁጥር 3 መሠረት የማወራረድ ሙሉ ሀላፊነት እና ተጠያቂነት አለባቸው፤

10/በውስጥ እና በውጭ ኦዲተሮች አማካኝነት የፕሮግራም እና የፋይናንስ ኦዲት ሲከናወን አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፤ የሚላከዉን የኦዲት ሪፖርቱ ተከትሎም አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የድርጊት መርሃ ግብር ያዘጋጃሉ እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃ በሦስት ወር ጊዜ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. የመተባበር ግዴታ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 መሰረት ይህ መመሪያ የሚመለከተው ማንኛውም አካል ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

13. ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱን ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

14. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ድህረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አህመድ ሺዴ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር

ጥር/2016

አባሪ 1፡ የመለኪያ ዝርዝር መስፈርት

| ተቁ | የአጻጸም መለኪያ መስፈርት | የሚሰጥ ውጤት ከ100% | የተሰጠው ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1. | **ገንዘቡ ተልኮ ሳይወራረድ ከሁለት ዓመት በላይ በውዝፍ ተይዞ ከሚገኘው የተወራረደ** | 35% | |
| ሀ | በውዙፍ ከሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ በሶስት ላወር ውስጥ 100 % ያወራረደ | 35% | |
| ለ | በውዙፍ ከሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ በሶስት ወር ውስጥ 75% እና በላይ ያወራረደ | 25% | |
| ሐ | በውዙፍ ከሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ በሶስት ወር ውስጥ 50%- 74 % ያወራረደ | 15% | |
| መ | በውዙፍ ከሚታየው ተሰብሳቢ ላይ ሂሳብ በሶስት ወር ውስጥ 25% - 49% ያወራረደ | 10% | |
| ሠ | በውዙፍ ከሚታየው ተሰብሳቢ ላይ ሂሳብ በሶስት ወር ውስጥ ከ25% በታች ያወራረደ | 0 | |
| 2 | **ገንዘቡ ተልኮ ሳይወራረድ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ድረስ በውዝፍ ተይዞ ከሚገኘው የተወራረደ** | 30% | |
| ሀ | በውዙፍ የሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ በሶስት ወር ውስጥ 100% እንዲወራረድ ከተደረገ፣ | 30% | |
| ለ | ከውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ በሶስት ወር ውስጥ 75% እና በላይ እንዲወራረድ ከተደረገ፣ | 25% | |
| ሐ | በውዙፍ የሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ በሶስት ወር ውስጥ 50%-74% እንዲወራረድ ከተደረገ፣ | 15% | |
| መ | ከውዝፍ ተሰብሳቢ ላይ ሂሳብ በሶስት ወር ውስጥ 25%-49% እንዲራረድ ከተደረገ፣ | 10% | |
| ሠ | ከውዝፍ ተሰብሳቢ ላይ ሂሳብ በሶስት ወር ውስጥ ከ25% በታች እንዲወራረድ ከተደረገ | 0 | |

| ተቁ | የአጻጸም መለኪያ መስፈርት | የሚሰጥ ውጤት ከ100% | የተሰጠው ውጤት |
|---|---|---|---|
| 3. | **በበጀት ዓመቱ የተላከና ስራ ላይ ውሎ በበጀት ዓመቱ ለተወራረደ ሂሳብ** | 25% | |
| ሀ | በበጀት ዓመቱ ውስጥ 100 % የተወራረደ፣ | 25% | |
| ለ | በበጀት ዓመቱ 75 % እና በላይ የተወራረደ፣ | 20% | |
| ሐ | በበጀት ዓመቱ ከ 50 %- 74 % የተወራረደ፣ | 15% | |
| መ | በበጀት ዓመቱ ከ 25%-49% የተወራረደ | 10% | |
| ሠ | በበጀት ዓመቱ ከ 25% በታች የተወራረደ | 0 | |
| 4 | በየወሩ የታረቀ የፋይናንስ ሪፖረት መላክ፣ የታረቀ statement of account፣ እንዲሁም የሂሣብ ማመዛዘኛ፣ ዝርዝር ተሰብሣቢ ሂሣብ፣ እና ሌሎች አባሪ ሪፖርቶችን በወቅቱ መላክ፤ | 10% | |
| | **የተገኘው አጠቃላይ ውጤት/ድምር** | 100% | |

## አባሪ 2፡ በጀት የሚለቀቅላቸው የክልል ጤና ቢሮዎች እና ፈጻሚዎች ዝርዝር

| ተ.ቁጥር. | የክልል ወይም ተቋም ስም |
|---|---|
| **የክልል እና ከተማ መስተዳድሮች ጤና ቢሮዎች** | |
| 1 | የትግራይ ጤና ቢሮ |
| 2 | የአፋር ጤና ቢሮ |
| 3 | የአማራ ጤና ቢሮ |
| 4 | የኦሮሚያ ጤና ቢሮ |
| 5 | የሶማሌ ጤና ቢሮ |
| 6 | የቤንሻንጉል ጉሙዝ ጤና ቢሮ |
| 7 | የደቡብ ኢትዮጵያ ጤና ቢሮ |
| 8 | የጋምቤላ ጤና ቢሮ |
| 9 | የሐረሪ ጤና ቢሮ |
| 10 | የሲዳማ ጤና ቢሮ |
| 11 | የደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ጤና ቢሮ |

| | |
|---|---|
| 12 | ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ጤና ቢሮ |
| 13 | የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳር ጤና ቢሮ |
| 14 | የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ |
| **የፌደራል ሆስፒታሎችና ተጠሪ ተቋማት** | |
| 1 | የኢትዮጵያ መድሀኒት አቅርቦት አገልግሎት |
| 2 | የኢትዮጵያ ጤና መድን አገልግሎት |
| 3 | ኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ባለስልጣን |
| 4 | የኢትዮጵ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት |
| 5 | አርማር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት |
| 6 | የኢትዮጵ ደምና ቲሹ ባንክ |
| 7 | አለርት ሆስፒታ |
| 8 | ቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ |
| 9 | አማኑኤል ሆስፒታል |
| 10 | ቅዱስጴጥሮስ ሆስፒታል |
| 11 | የኢትዮጵያ የሰው ሰራሽ እና አካል ድጋፍ አገልግሎት |
| 12 | ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል |
| **የህክምና ትምህርት የሚሰጡ ዩኒቨርስቲዎች** | |
| 1 | አዳማ ጀነራል ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ |
| 2 | አዳማ  ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ |
| 3 | አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ |
| 4 | አዲግራት ዩኒቨርሲቲ |
| 5 | አክሱም ዩኒቨርሲቲ |
| 6 | አምቦ ዩኒቨርሲቲ |
| 7 | አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ |
| 8 | አርሲ ዩኒቨርሲቲ |
| 9 | ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ |
| 10 | ደብረ ብርሀን ዩኒቨርሲቲ |
| 11 | ደብረ  ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ |

| | |
|---|---|
| 12 | ደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ |
| 13 | መከላከያ ዩኒቨርሲቲ |
| 14 | ዲላ ዩኒቨርሲቴ |
| 15 | ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ |
| 16 | ጎንደር ዩኒቨርሲቴ |
| 17 | ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ |
| 18 | ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ |
| 19 | ጂግ ጂጋ ዩኒቨርሲቲ |
| 20 | ጂማ ዩኒቨርሲቲ |
| 21 | መዳላቡ ዩኒቨርሲቲ |
| 22 | መቀሌ ዩኒቨርሲቲ |
| 23 | ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ |
| 24 | ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ |
| 25 | ወለጋ ዩኒቨርሲቲ |
| 26 | ቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ |
| 27 | ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ |
| 28 | ወላይታ ዩኒቨርሲቲ |
| 29 | ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ |
| 30 | ወሎ ዩኒቨርሲቲ |
| 31 | ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ |
| 32 | ወሎ ዩኒቨርሲቲ |
| 33 | የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ |
| 34 | ይርጋለም ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ |